# ትምህርት 1

- እዚህ የመጣሁት ለምንድነው?

- እዚህ የመጣሁት ልጐዳችሁ ነው?
- አይደለም።

- እዚህ የመጣሁት ቤተሰባችሁን ወይም ጓደኞቻችሁን ልጐዳ ነው?
- አይደለም።

- እዚህ የመጣሁት መሬታችሁን ልወስድ ወይም ከብቶቻችሁን ልሰርቅ ነው?
- አይደለም።

- ታዲያ እዚህ የመጣሁት ለምንድነው?
- እዚህ የመጣሁት ለአንድ ጉዳይ ብቻ ነው።

- እዚህ የመጣሁት በዚህ ዓለም እጅግ አስፈላጊ የሆነውን መልእክት ልነግራችሁ ነው።

- እዚህ የመጣሁት የእግዚአብሔርን መልእክት ልነግራችሁ ነው።

- እዚህ የመጣሁት የነጮችን መልእክት ልነግራችሁ አይደለም።
- እዚህ የመጣሁት የጥቁር ሕዝቦችን መልእክት ልነግራችሁ አይደለም።

- እዚህ የመጣሁት የእግዚአብሔርን መልእክት ብቻ ልነግራችሁ ነው።

- መሪያችሁ ለአስፈላጊ ጉዳይ ሁላችሁንም ቢጠራችሁ ትመጣላችሁ አይደል?

- አዎን ትመጣላችሁ።
- ለምንድን ነው የምትመጡት?

- ምክንያቱም መሪያችሁ የሚነግራችሁ መልእክት አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

- የመሪ መልእክት አስፈላጊ ነው ነገር ግን ከመሪ መልእክት እጅግ የሚበልጥ መልእክት አለ።

- ከመሪ መልእክት የሚበልጥ መልእክት የማን መልእክት ነው?
- የእግዚአብሔር መልእክት ነው።

- በዚህ ዓለም እጅግ አስፈላጊ የሆነው መልእክት የማን መልእክት ነው?

- የእግዚአብሔር መልእክት ነው።

- የእግዚአብሔር መልእክት በዚህ ዓለም እጅግ አስፈላጊ መልእክት የሆነው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር በፍጹም ስለማይዋሽ ነው።

- እግዚአብሔር ሁል ጊዜ እውነትን ብቻ ስለሚናገር ነው።

- ከሰዎች መካከል ዋሽቶ የማያውቅ አለ?
- የለም ሁሉም ሰው ዋሽቷል።

- ከእናንተ መካከል ዋሽቶ የማያውቅ አለ?
- የለም ሁላችሁም ዋሽታችኋል።

- ከዚህ በፊት እኔም ዋሽቼአለሁ።
- ነጭ ሁሉም ዋሽቶአል።

- ጥቁር ሁሉም ዋሽቶአል።
- ሁሉም ሰው ዋሽቶአል።

- ዋሽቶ የማያውቅ ማን ነው?

- እግዚአብሔር ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር ዋሽቶ ስለማያውቅ፤ እውነቱን ሊነግረን የሚችለው እርሱ ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር በፍጹም ዋሽቶ ስለማያውቅ ስለ ራሱ እውነቱን ሊነግረን የሚችለው እርሱ ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር ፈጽሞ ዋሽቶ ስለማያውቅ የእግዚአብሔር መልእክት በዚህ ዓለም እጅግ አስፈላጊ መልእክት ነው።

- ለወንዶች የእግዚአብሔር መልእክት በእርሻ ቦታ ከመሥራት የበለጠ አስፈላጊ ነው።

- ለምን?
- ምክንያቱም ወንዶችን ሁሉ ከሞት ማዳን የሚችለው የእግዚአብሔር መልእክት ብቻ ስለሆነ ነው።

- ለሴቶች የእግዚአብሔር መልእክት ምግብ ከማብሰል የበለጠ አስፈላጊ ነው።

- ለምን?
- ምክንያቱም ሴቶችን ሁሉ ከሞት ማዳን የሚችለው የእግዚአብሔር መልእክት ብቻ ስለሆነ ነው።

- ለልጆች የእግዚአብሔር መልእክት ከጨዋታ የበለጠ አስፈላጊ ነው።
- ለምን?

- ምክንያቱም ልጆችን ሁሉ ከሞት ማዳን የሚችለው የእግዚአብሔር መልእክት ብቻ ስለሆነ ነው።

- የእግዚአብሔር መልእክት የሚገኘው የት ነው?

- የእግዚአብሔር መልእክት የሚገኘው በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ ነው።

- የእግዚአብሔር መጽሐፍ ምን ይባላል?
- የእግዚአብሔር መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ይባላል።

- የእግዚአብሔር መልእክት በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ እንዴት ተጻፈ?

- እግዚአብሔር ራሱ የራሱን መልእክት በመጽሐፍ ሊጽፍ ይችል ነበር ሆኖም ግን ይህን አላደረገም።

- ከረጅም ዘመናት በፊት እግዚአብሔር ጥቂት ሰዎችን መረጠ ቃሉንም በእነዚህ ሰዎች ልብ ውስጥ አኖረ።

- ከዚያም እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ ጻፉት።

- እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የጻፉት የራሳቸውን ቃል ነው?
- የራሳቸውን ቃል አይደለም።

- እነዚህ እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች የራሳቸውን ቃል አልጻፉም።
- እነዚህ ሰዎች የጻፉት የእግዚአብሔርን ቃል ነው።

- እነዚህ እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች የጻፉት በትክክል የእግዚአብሔርን ቃል ነው።

- እግዚአብሔር ቃሉን በእርሱ መጽሐፍ እንዲጽፉ አርባ ያህል ሰዎችን መረጠ።

- እነዚህ የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት ሰዎች ሁሉም የኖሩት በተመሳሳይ ጊዜ ነበር?

- አይደለም።
- እነዚህ የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት ሰዎች ሁሉም በተመሳሳይ ጊዜ አልኖሩም።

- ሁሉንም የእግዚአብሔር ቃል ጽፎ ለማጠናቀቅ ምን ያህል ጊዜ ፈጀ?

- እነዚህ እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች ቃሉን ጽፈው ለማጠናቀቅ 1,600 ዓመታት ፈጅቶባቸዋል።

- እነዚህ እግዚአብሔር ቃሉን እንዲጽፉ የመረጣቸው ሰዎች እነማን ነበሩ?

- እግዚአብሔር ቃሉን እንዲጽፉ የመረጣቸው ሰዎች አይሁዶችና አንድ ግሪካዊ ነበሩ።

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት በምን ቋንቋ ነበር?
- በአይሁዶችና በግሪኮች ቋንቋ ነበር።

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት በእንግልእኛ ነበር?
- አይደለም

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት በአማርኛ ነበር?
- አይደለም።

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት በኦሮምኛ ነበር?
- አይደለም።

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት በራሳቸው ቋንቋ ነበር።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ቃሉን እንዲጽፉ የመረጣቸው ሰዎች አይሁዶችና አንድ ግሪካዊ ስለነበሩ ነው።

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የጻፉት በአይሁዶችና በግሪኮች ቋንቋ

ነበር።
- ከብዙ ጊዜ በኋላም ሌሎች ሰዎች ወደ አይሁድ ምድር መጡ የእግዚአብሔርን ቃል አነበቡ፤ ወደ የራሳቸውም ቋንቋ ተረጐሙት።

- የእግዚአብሔር ቃል በብዙ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

- የእግዚአብሔር ቃል በእናንተም ቋንቋ ተተርጐሟል፤ እየተተረጐመም ነው።

- በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል መካከል ስንቱ እውነት ነው?

- ሁሉም እውነት ነው።

- በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የሚገኘው ሁሉም የእግዚአብሔር ቃል እንዴት እውነት ሊሆን ቻለ?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር በፍጹም ስለማይዋሽ ነው።

- እግዚአብሔር እውነትን ብቻ ስለሚናገር ነው።

- በእግዚአብሔር መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙትን የእግዚአብሔርን ቃሎች የምናምነው ለምንድነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር በፍጹም ስለማይዋሽ ነው።
- እግዚአብሔር እውነትን ብቻ ስለሚናገር ነው።

- ሁልጊዜ እውነትን ብቻ የሚናገር ማን ነው?
- እግዚአብሔር ነው

- እኔ በእግዚአብሔር መጽሐፍ የሚገኘውን የእግዚአብሔርን ቃል አንብቤ ሁሉም የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን አውቄያለሁ።

- እናንተም የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰሙ የእግዚአብሔር ቃል እውነት መሆኑን ታውቃላችሁ።

- የዚህ ምክንያቱ እግዚአብሔር በፍጹም ስለማይዋሽ ነው።
- የዚህ ምክንያቱ እግዚአብሔር እውነትን ብቻ ስለሚናገር ነው።

- እግዚአብሔር ብዙ የሚነግረን ነገር አለው።
- ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ለእናንተ ለማስተማር ብዙ ቀን ያስፈልጋል።

- አንድ ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- የእርሻን ሥራ ለማወቅ ምን ያህል ቀናት ይወስዳል?
- አዎ ብዙ ቀናት ይወስዳል።

- የእርሻን ሥራ ለማወቅ ብዙ ቀናት የሚወስደው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ስለ አስተራረስ ልናውቃቸው የሚገቡን ብዙ እውነቶች ስላሉ ነው።

- መሬቱን እንዴት ለዘር እንደምታዘጋጁ ማወቅ አለባችሁ።

- እንዴት አድርጋችሁ ዘር መዝራት እንዳለባችሁ ማወቅ አለባችሁ።

- እንዴት አድርጋችሁ አረም ማረም እንዳለባችሁ ማወቅ አለባችሁ።

- የደረሰውን ሰብል እንዴት እንደምትሰበስቡ ማወቅ አለባችሁ።

- የእርሻን ሥራ ለማወቅ ብዙ ቀን እንደሚያስፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለመማርም ብዙ ቀን ያስፈልጋል።

- ለዚህም ምክንያቱ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብዙ እውነቶች ስላሉ ነው።

- የእግዚአብሔርን ቃል ለብዙ ቀናት ካደመጣችሁ ስለ እግዚአብሔር ብዙ እውነቶችን ትማራላችሁ።

- ሌላ ምሳሌ ልንገራችሁ፡

- በየቀኑ ምግብ ትበላላችሁ?
- አዎ ትበላላችሁ።

- በየዕለቱ ምግብ የምትበሉት ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም ሰውነታችሁ በየዕለቱ ምግብ ስለሚፈልገው ነው።

- ሰውነታችሁ በየዕለቱ ምግብ እንደሚያስፈልገው ሁሉ የእግዚአብሔርንም ቃል በየዕለቱ ማዳመጥ ያስፈልጋችኋል።

- በየቀኑ ካልተመገባችሁ ምን ትሆናላችሁ?
- አዎ ትሞታላችሁ።

- የእግዚአብሔርን ቃል በየዕለቱ ካላዳመጣችሁም እንዲሁ ትሞታላችሁ።

- አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል የማያውቁት ለምንድን ነው?

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለማዳመጥ ስለማይፈልጉ ነው።

- እነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለማመን ስለማይፈልጉ ነው።

- የእግዚአብሔርን ቃል በየቀኑ የምታደምጡ ከሆነ ደስተኛ ትሆናላችሁ።

- የእግዚአብሔርን ቃል በየቀኑ ካላዳመጣችሁ ደስተኞች አትሆኑም።

- የእግዚአብሔርን ቃል በየቀኑ ለማዳመጥ እንደምትመጡ ተስፋ አደርጋለሁ።